# 181st Semiannual General Conference
# Priesthood Session, October 1, 2011

## ብቻችሁን ለመቆም አትፍሩ

በፕሬዘደንት ቶማስ ኤስ ሞንሰን

ውድ ወንድሞቼ፣ ከእናንተ ጋር በዚህ ምሽት መገኘት ታላቅ ክብር ነው። የእግዚአብሔር የክህነት ስልጣን የያዝነው ታላቅ ጓደኝነትና የወንድሞች ግንኙነት አለን።

በትእናቃ 121 ቁጥር 36 ውስጥ እንደምናነበር፣ "የክህነት ስልጣን መብቶች እና የሰማይ ሀይሎች የማይነጣጠሉ ናቸው።" "ከሰማይ ሀይሎች ጋር የማይነጠ" የክህነት ባለስልጣን ለመሆን የተሰጠን ምን አይነት አስደናቂ ስጦታ ነው። ይህም ውድ ስጦታ ልዩ በረከቶችን ብቻ ሳይሆን መለኮታዊ ሀላፊነቶችንም ይዞ የሚመጣ ነው። ላለን ለክህነት ስልጣን ብቁ በመሆን መኖር አለብን። ወደ ጥፋታችን መንገዶች በሚመሩን ነገሮች በተከበብንበት ጊዜ ነው የምንኖረው። እንደዚህ አይነት መንገድን ለማስወገድ ውሳኔና ብርቱ መሆን ያስፈልገዋል።

የብዙዎች ሰዎች ምግባረ ጥሩነት መሰረት እንደኛ አይነት የነበረበትን ጊዜ እናንተእንደምታስታውሱት እኔም አስታውሰዋለሁ። ይህም አሁን እውነት አይደለም። በ2008ዓ/ም ስለነበረ ጥናት በ New York Times ጋዜጣ ውስጥ አንብቤ ነበር። ስለህብረተሰብ የሚያጠና የኖተርዴም ፕሮፌሰር በአሜሪካ ከ230 ወጣቶች ጋር ጥልቅ የቃል ንግግር በማድረግ ጥናቱን አከናውኖ ነበር። ውጤታው በአለም ውስጥ ሁሉ አንድ እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ።

ከአንቀጹ ትንሽ ክፍሉን ከእናንተ ጋር እካፈላለሁ።

‘ስለትክክል እና ትክክል ስላልሆነው፣ ስለ ምግባረ ጥሩነት ያለው መጥፎ ምርጫዎችና ስለህይወት ትርጉም ቃል የሚጠየቁት ተጠይቀው ነበር። መልስ በሰጡትም፣ ... ወጣት ሰዎች ትርጉም ያለው መልስ ለመስጠት ሲታገሉ ትመለከታላችሁ። ነገር ግን ይህን ለማድረግ የሚመልሱበት የቋንቋ ችሎታ ወይም ቃላት አልነበራቸው።

"ምግባረ ጥሩነትን በሚመለከት ሁለት መጥፎ ምርጫዎች ላይ ለመምረጥ ስለነበረባቸው አጋጣሚ ሲጠየቁ፣ ሁለት ሶስተኞቹ ወጣቶች መልስን ለመስጠት አልቻሉም ወይም አንዳንድ መኖሪያ ቦታዎችን ለመከራየት እንደሚችሉ ወይም መኪና በሚያቆመብት ቦታ ለመክፈል በቂ ገንዘድ እልዳላቸው አይነት የገለጿቸው ነገሮች ከስነ ምግባር ጋር የተገኘኙ አልነበረም።"

አንቀጹም ቀጥሏል፥

"በደጋጋሚ ሁሉም የተመለሱበት መልስ ቢኖር፣ የምግባረ ጥሩነት ምርጫዎች የግለሰብ ምርጫ እንደሆነ ነው። መልሱም በአብዛኛው ጊዜ፣ ‘የግለሰብ ምርጫ ነው፣ ይህም የግለሰብ ሀላፊነት ነው። እኔ ይህ ይሁን ለማለት ማን ነኝ።’

"ለባለስልጣን ስይታሰብበት ክብር መስጠትን በማስወገድ፣ ብዙዎቹ ወጣት ሰዎች ‘እንደሚያስደስተኝ የማስብበትን ወይን እንደሚሰማኝ አደርጋለሁ። በውስጤ ከሚሰማኝ በላይ ምን ማድረግ እንዳለብኝ የማውቅበት ምንም መንገድ የለም’ ወደሚለው ሄደዋል።"

የቃል ጥያቄውን ያከናወኑት ያነጋገሯቸው ብዙዎቹ ወጣት ሰዎች "በትምህርትቤት፣ በድርጅቶች ወይም በቤተሰብ የምግባረጥሩነት አስተሳሰብን ለማሳደግ ምንም መንጭ ተሰጥቷቸው እንዳልነበረ" በትኩረት ተናግረዋል።

ወንድሞች፣ ድምጼን የሚሰማው ማንም ምኑ ትክክለኛ ተግባር እንደሆነ እና የትኛው መጥፎ ተግባር እንደሆነ መምታታት አይገባውም፣ ወይም እንደ እግዚአብሔር የክህነት ባለስልጣኖች ምን እንደሚጠበቅብን መጠራጠር አይገባቸውም። የእግዚአብሔርን ህግጋት ተምረናል እናም በመማር እንቀጥላለን። በማንኛውቦታ ነገሮችን ብትሰሙወይም ብታዩው፣ እነዚህ ህግጋት አይቀየሩም።

ቀን በቀን ስንኖር፣ እምነታችን የሚፈተንበት ጊዜ እንደሚመጣየተረጋገጠነወ። በሌሎች ተከብበን፣ እንደ ታናሽ የምንሆንበት ወይም የትኛውተቀባይ እንደሆነ እና እንዳልሆነ በብቻችን የቆምንበት ጊዜ ይኖራል። ምንም እንኳን ብቻችንን ብንሆንም ለምናምነውበፅኑነት ለመቆም ብርቱ ነን?እንደ እግዚአብሔር የክህነት ባለስልጣኖች፣ በብርቱነት የሚያጋጥመንን ፈተናዎች ለመቋቋም መቻላችን አስፈላጊ ነው። ቴንሰን ያለውን ቃላት አስታውሱ፥ "ልቤንጹህ ስለሆነ፣ ጥንካሬዬ እንደ አስር ሰውጥንካሬ ነው።"

ተዋቂ ሰዎች ሀይማኖትን እና በልዩም ቤተክርስቲያኗን የማሳለቅ ልምድ አላቸው። ምስክራችን በፅኑነት የተተከለ ከሆነ፣ እንደዚህ አይነት ትቾታ በእምነታችን ላይ ጥርጣሬ እንዲኖረን ወይም ከውሳኔአችን እንድንወላወል ሊያደርገን አይችልም።

በ1ኔፊ 8ውስጥ በሚገኘውሌሂ ስለህይወት ዛፍ ባየውራዕ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነ የምናውቀውን የህይወት ዛፍ ፍሬን እስከሚበሉ ድረስ የብረት በትርን የያዙትን ከሌሎች ጋር አይቶ ነበር። ከእዚያም፣ በሚያሳዝን ሁኔታ፣ ፍሬውን ከበሉ በኋላ፣ ጣትን እያጠቆሙበሚሳለቁባቸውየሰው ልጆችን ትቢት በሆነው "በታልቁ ህንጻዎች" ውስጥ ባሉት ምክንያት አፈሩ፤ እናም ወደ ተከለከለውመንገድ ወደቁ እናም ጠፉ። መሳለቅና ማፌዝ ምን አይነት የጠላት ሀይለኛ መሳሪያ ነው!እንደገናም ወንድሞች፣ በእንደዚህ አይነት ቅዋሜ በጥንካሬና በፅኑነት ለመቆም ብርቱ ነን?

ለማምንበት ብርቱ ለመሆን አጋጣሚለመጀመሪያ ጊዜ አጋጣሚየነበረኝ በሁለተኛው የአለምጦርነት መጨረሻ ላይ በዩኤስ የባህር ሀይል ውስጥ በማገለግልበት ጊዜ ነበር።

የባህር ሀይል ማሰልጠኛ ቦታለእኔ ወይም በእዚያ ለነበሩት ሁሉ ቀላል አጋጣሚ አልነበረም። ለመጀመሪያውሶስት ሳምንቶች ህይወቴ በአደጋ ላይ እንዳለ አምኜ ነበር። የባህር ሀይል ሊያሰለጥነኝ ሳይሆን ሊገድለኝ ፈልጎ ነበር።

ከመጀመሪያውሳምንት በኋላ እሁድ ሲመጣ አስታውሳለሁ። ከአለቃችን የሚያስደስት ዜና ተቀበልን። በካሊፎርኒያ ንፋሳ ውስጥ ቆመን፣ ትእዛዙን አዳመጥን፥ "ዛሬ ከእኔ በስተቀር ሁሉም ሰውወደ ቤተክርስቲያን ይሄዳል። እኔ ግን እዝናናለሁ።" ከእዚያ መንዲህ ብሎ ጮኸ፣ "ካቶሊኮቹ ወደ ዲካንተር ስፍራ ትሰበሰባላችሁ---እናም እስከ ሶስት ሰዓት ድረስ አትመለሱ፣ ወደፊት ሂዱ!" ብዙዎቹ ሄዱ። ከእዚያም የሚቀጥለውን ትእዛዝ ሰጠ፣ "አይሁዶች፣ በሄንሪ ስፍራ ትሰበሰባላችሁ---እናም እስከ ሶስት ሰዓት ድረስ አትመለሱ፣ ወደፊት ሂዱ!" ቁጥራቸውየቀነሰ ሰዎች ሄዱ። ከእዚያም "የቀራችሁት ፕሮቴስታንቶቹ በፈረጎት ስፍራ ትሰበሰባላችሁ---እናም እስከ ሶስት ሰዓት ድረስ አትመለሱ፣ ወደፊት ሂዱ!"

፣ ወዲያውም ይህ ሀሳብ በአዕምሮዬ አለፈ፣ "ሞንሰን፣ አንተ ካቶሊክ አይደለህም፤ አይሁድ አይደለህም፤ ፕሮቴስታንት አይደለህም። አንተ ሞርሞን ነህ፣ ስለዚህ የትም

አትሂድ!” በጣም ብቸኛነት እንደተሰማኝ በእርግጥ እነግራችኋለሁ። ብርቱ እና ውሳኔ ያደረግሁኝ፣ ብሆንም፣ ብቸኛ ነበርኩኝ።

ከእዚያም አልቃውሰምቼውየ ማላውቀውን መልካምንግግር ሲናገር ሰማሁ። ወደ እኔ ተመለከተና እንዲህ ጠየቀኝ፣ “እናንተ እራሳችሁን ምን ብላችሁ ትጠራላችሁ?” እስከዚያ ጊዜ ድረስ ከኋላዬ ሌላ ሰውቆሞእንደነበር አላወቅኩምነበር። ሁላችንም በአንድነት “ሞርሞኖች!” ብለን መለስን። ዞር ስል እና ቁጥራቸውትንሽ የነበረው የባህር ሀይል ወታደሮችን ሳይ ልቤን የሞላውን ደስታ ለመግለፅ አልችልም።

አለቃችንምጸጉሩን አከከና የተምታታ መሰለ፣ ግን በመጨረሻም፣ “የምትሰበሰቡበትን ቦታ ለማግኘት ሂዱ። እና እስከ ሶስት ሰዓት ድረስ አትመለሱ፣ ወደፊት ሂዱ!” አለን።

በሰልፍ ስንሄድም፣ በመጀመሪያ ክፍል እድሜዬ የተማርኩትን መዝሙር አሰላሰልኩኝ፥

ሞርሞን ለመሆን ድፈሩ፤
ብቻችሁን ለመቆም ድፈሩ።
ፅኑ አላማእንዲኖራችሁ ድፈሩ፤
ለማስታወቅም ድፈሩ።

አጋጣሚዬ ከጠበቅኩት የተለየ ቢሆንም፣ የሚያስፈልግ ቢሆን ኖሮ ብቻዬን ለመቆም ፈቃደኛ ነበርኩኝ።

ከእዚያ ቀን ጀምሮ ከኋላዬ የቆሙማንምያልነበሩበት ጊዜ ስለነበረብቻዬን ቆሜ የበረበት ጊዜ ነበር። ጠንካራ እና እውነተኛ ለመሆን፣ አስፈላጊ ከሆነ ለሀይማኖቴ ለመከራከር ሁልጊዜምስለተዘጋጀሁ ከረጅምጊዜ በፊት ስለወሰንኩኝ ምስጋና አለኝ።።

ወደፊት ላለን ስራ ብቁ እንዳልሆንን እንዳይሰማን፣ በ 1987 ዓ/ም ፕሬዘደንት ቤንሰን ለካሊፎርኒያ አባላት የተናገሩትን ከእናተ ጋር ልካፈል። እንዲህምአለች፥ “በሁሉም ዘመናት፣ ነቢያት ወደ ዘመናችን ተመልከተዋል። ብዙ ቢልዮን የሆኑት ሙታን እና ገና ያልተወለዱትምእየተመለከቱን ናቸው። እናንተ የተመረጣችሁ ትውልዶች ናችሁ። ለስድስት ሺህ አመት እናንተ ከጌታ ዳግምምፅዓት በፊት በመጨረሻውቀናት እንድትመጡ እግዚአብሔር የጠበቃችሁ ናችሁ። አንዳንዶች ይወድቃሉ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር መንግስት አለቃውን በሰላምእስከሚቀበል ድረስ ይጸናል። ይህ ትውልድ ጌታ ምድርን በውሀ ካጸዳበት ከኖህ ዘመን ኃጢአት ጋር የተመሳሰለ ቢሆንም፣ ከዚህ ዘመን ጋር ታላቅ ልዩነት አለ። ይህምለመጨረሻውቀናት እግዚአብሔር መንግስትን በድል ለመሸከም የሚረዱ ጠንካራ ልጆቹን ጠብቋል።”

አዎን ወንድሞች፣ እኛ የእርሱ ጠንካራ ልጆች ነን። ሀላፊነታችንምየሰማይ አባታችን ለሚሰጠን ድንቅ በረከቶች በሙሉ ብቁ ለመሆን ነው። የትም ብንሄድ፣ የክህነት ስልጣናችን አብሮን ይሄዳል። በቅዱስ ቦታዎች ቆመናል? ለእናንተ ብቁ ባልሆኑ ነገሮች በመሄድ ወይም በመሳተፍ እራሳችሁን እና የክህነት ስልጣናችሁን በአደጋ ላይ ከማድረጋችሁ በፊት፣ ስለ ውጤታውአስቡበት። እያንዳንዳችን የአሮናዊ የክህነት ስልጣን ተሰጥቶናል። በዚህምእያንዳንዳችን የምላእክት አገልግሎት ቁልፎች ሀይል ተቀብለናል። ፕሬዘደንት ሒንክሊ እንዳሉት፥

“በእናንተ እና ለእናንተ ጥቅምበሚያገለግሉት መላእክት መካከል መጋረጃ የሚያስቀምጥ ምንምነገር ለማድረግ አይገባችሁም።

“በምንም መንገድ ስነ ምግባር የለሽ ለመሆን አትችሉም። የማትታመኑ ለመሆን አትችሉም። ለማታለልና ለመዋሸት አትችሉም። የእግዚአብሔርን ስምበከንቱ ለመጠቀም ወይም መጥፎ

ቋንቋዎችን ለመጠቀም እና የመላእክት አገልግሎት ለማግኘት መብት ሊኖራችሁ አትችሉም።”

በጎዞአችሁ ማንኛችሁም ከተሰናከላችሁ፣ መመለሻ መንገድ እንዳለ እንድታውቁ እፈልጋችኋለሁ። ይህም መንገድ ንስሀ መግባት ነው። አዳኛችን ይህን የተባረከ ስጦታ ለእናንተ እና ለእኔ ለመስጠት ህይወቱን አሳልፎ ሰጥቷል። ይህም ቢሆን ንስሀ መግባት ቀላል ባይሆንም፣ ቃል ኪዳኖች እውነት ናቸው። እንደተነገርነው፣ “ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች።” “እኔም አላስታውሳቸውም።”

“ሁሉንም ትእዛዛት አላከብርም እናም ማድረግ የሚገባኝን በሙሉ አላደርግም፣ ህይወቴ ግን ደህና ነው። ኬኩን ኖሮኝ ልበላውም እችላለሁ” ብላችሁ የምታስቡ አንዳንዶች አላችሁ። ወንድሞች፣ ይህ ለረጅም ጊዜ እንደማይሰራ ቃል እገባላችኋለሁ።

ሁሉንም እንደፈለገው ለማግኘት ካሰበ ሰው ባለፉት ወሮች ደብዳቤ አገኘሁ። አሁን ንስሀ ገብቷል እናም ህይወቱን በወንጌል መሰረታዊ መመሪያዎችና በትእዛዛት ተከታይ አድርጓል። የስህተተኛው አስተሳሰብ ምሳሌ ስለሆነ፣ ከደብዳቤው ክፍል ላንብብላችሁ፥ “(በአስቸጋሪ ሁኔታ) አዳኝ “ማንም ሰው ሁለት ጊታዎች ለማገልገል አይችልም፥ አንዱን ጠልቶ ሌላውን ይወድዳል፤ አለበለዚያ አንዱን ይዞ፣ ሌላውን ይጠላል። እግዚአብሔርንና ገንዘብን ለማገልገል አትችልም” ያለበት በጣም ትክክል እንደሆነ ተማርኩኝ። ሁለቱንም ለማድረግ በጣም ጣርኩኝ። በመጨረሻም፣ ሰይጣን በሚያታልልበት፣ እና በምሽቱ ለሚያምኑት የሚሰጠውን ባዶነት፣ ጭለማና ብቸኝነት በሙሉ አገኘሁ።”

ጠንካራ ለመሆንና ትክክል ወዳልሆነው የሚጎትቱን ሀይሎችን ወይም በስህተተኛው መንገድ እንድንሄድ የሚያበረታቱንን ድምጾች ለመቋቋም፣ የእራሳችን ምስክር ያስፈልገናል። እናንተ 12 ወይም 112 ብትሆኑም፣ ለእራሳችሁ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል እውነት እንደሆነ ለማወቅ ትችላላችሁ። መፅሐፈ ሞርሞንን አንብቡ። የሚያስተምረውን አሰላስሉበት። የሰማይ አባትን ይህ እውነት እንደሆነ ጠይቁት። “በቅን ልባችሁ፤ ከእውነተኛ ፍላጎት፣ በክርስቶስ አምናችሁ ከጠየቃችሁት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እውነቱን ይገልፅላችኋል” የሚል ቃል ኪዳን አለን።

መፅሐፈ ሞርሞን እውነት እንደሆነ ስታውቁ፣ ጆሴፍ ስሚዝ በእርግጥም ነቢይ እንደሆነና እግዚአብሔር የዘለአለማዊ አብንና ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳየ በመከተል ይታወቃል። ይህም ወንጌሉ በእነዚህ በኋለኛው ቀናት በጆሴፍ ስሚዝ በኩል፣ ከአሮናዊና ከመልከ ጸዴቅ የክህነት ስልጣን ጋር፣ በዳግም እንደተመለሰም ይታወቃል።

አንዴ ምስክር ካለን፣ ይህን ምስክር ከሌሎች ጋር የመካፈል ሀላፊነት አለብን። ብዙዎቻችሁ ወንድሞች በአለም ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች በሚስዮን አገልግላችኋል። ብዙዎቻችሁ ወጣት ወንዶች ገና ታገለግላላችሁ። ለዚህ እድል እራሳችሁን አዘጋጁ። ለማገልገ ብቁ ሁኑ።

ወንጌሉን ለመካፈል ከተዘጋጀን፣ “በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁዋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ” በማለት ሀዋርያው ጴጥሮስ ያበረታታንን መልስ ለመስጠት እንችላለን።

ምንም እንኳን ይህን ለማድረግ መቼ እንደምንጠራ ባናውቀውም፣ ሀይማኖታችንን ለመካፈል በህይወታችን ሁሉ እድል ይኖረናል። በ1975 ዓ/ም በሚያትሙቢዝነስ ውስጥ እየሰራሁ እያለሁና ወደ ዳላስ ቴክሳስ በስብሰባ ንግግር እንዳደርግ እንድሄድ በጠጠራሁበት ጊዜ እንደዚህ አይነት እድል አጋጠመኝ። ከስብሰባው መጨረሻ በኋላ፣ ከተማዎችን ለማየት በአውቶቡስ ተጓዝኩኝ። የተለያዩ ቤተክርስቲያኖችን እያየን

ስናልግ፣ መኪና ነጂው እንዲህ ይል ነበር፣ “በግራ በኩል የሜተድስት በኢተክርስቲያንን ታያላችሁ፣” ወይም “በቀኝ በኩል የካቶሊክ ቤተክርስቲያን አለ።”

በኮረብታ ላይ ያለውን የቀይ ድንጋይ ህንጻ ስናልፍ፣ መኪና ነጂው “ያም ህንጻ ሞርሞኖች ይሚሰበሰቡበት ነው” አለ። በአውቶቡሱ መደኋላ የተቀመጠችም ሴት መኪና ነጂውን “ስለሞርሞኖች ተጨማሪ ልትነግረን ትችላለህ?” ብላ ጠየቀችው።

ነጂው አውቶቡሱን አቆመና ከመቀመጫው ዞሮ እንዲህ መለሰ፣ “ስለሞርሞን የማውቀው ነገር ቢኖር በቀዩ ሸከላ ቤተክርስቲያን እንደሚሰበሰቡ ነው። ስለሞርሞኖች የሚያውቅ ሰው በዚህ አውቶቡስ አለ? ብሎ ጠየቀ።

ሰው መልስ እንዲሰጥ ጠበቅኩኝ። በእያንዳንዱ ሰው ፊት ላይ ያለውን አመላካከት እያምወቅ ምልክትን ወይም መልስ የመስጠት ፍላጎትን ለማየት ተመለከትኩኝ። “በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን

ለሚጠይቁዋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ” ብሎ ሀዋርያው ጴጥሮስ የመከረውን ማድረግ የእኔ ሀላፊነት እንደሆነ ገባኝ። በተጨማሪም “ለውሳኔ ጊዜ ሲመጣ፣ የመዘጋጃ ጊዜ አልፏል” የሚለው አባባል እውነት እንደሆነ ገባኝ።

ለሚቀጥለው 15 ደቂቃ፣ በአውቶቡስ ውስጥ ከነበሩት ጋር ስለቤተክርስቲያኗ እና ስለእምነታችን ምስክሬን ለመካፈል እድል ነበረኝ። ለምስክሬ እና ለመመስከር የተዘጋጀሁ በመሆኔ ምስጋና ተሰምቶኛል።

በልቤ እና በነፍሴ በሙሉ የክህነት ስልጣን ያለው እያንዳንዱ ሰው ያን የክህነት ስልጣን እንዲያከብር እናም በተሰጠበት ጊዜ ለተላለፈው ታማኝነት እውነት እንዲሆን እጸልያለሁ። የክህነት ባለስልጣኖች የሆንነው እያንዳንዳችን በምናምንበት ለመቆም ብርቱና የተዘጋጀን እንሁን፣ እናም በብቻችን ከቆምንም፣ ይህንንም በብርቱነት፣ ከሰማይ አባታችን ጋር አብረን ስንቆም በምንም በብቻችን እንዳልሆንን ባለን እውቀት እንጠናከር።

“የክህነት ስልጣን መብቶች እና የሰማይ ሀይሎች የማይነጣጠሉ ናቸው” የሚለውን የተሰጠንን ታላቁን ስጦታ ስናሰላስልበት ይህን ለመከላከልና ለመጠበቅ እናም ለታላቁ ቃል ኪዳኖች ብቁ ለመሆን ለዘለአለም እንወስን። በ3ኔፊ ውስጥ “ስለዚህ፣ ለዓለም ያበራ ዘንድ ብርሃናችሁን ከፍ አድርጉ። እነሆ፣ እኔ ሳደርግ የተመለከታችሁትም፣ እናንተ ከፍ የምታደርጉት ብርሃን ነኝ” ብሎ አዳኝ የሰጠንን መመሪያ እንከተል።

ያን ብርሀን እንድንከተል እና አለም ሁሉ እንዲያዩት ከፍ እንድታደርጉ የምጸልየው በኢየሱስ ክርስቶስ ስምን ነው፣ አሜን።